# DAWIT DERSOLIGN



## 3 – 18 December 2022

Dawit Dersolign doesn't call himself an artist. As a child, he experimented with artmaking, woodwork, and metalwork, but didn't continue these practices as he grew up. In 1986, as a teenager living in a refugee camp in Sudan, Dawit reconnected with art while working with the International Rescue Committee. For two years he painted educational imagery for the Education Resource Centre. Dawit didn't start making work again until 2017, when he began working at Life Raft Tasmania. He saw possibility in the array of waste materials produced at his workplace, and began experimenting with reusing and recycling the materials in creative ways.

Dawit's approach to artmaking is fused with experiment, discovery and an interest in playfulness over outcome. He says of his work that he often begins with the materials he has on hand, always found and recycled, and sees where he ends up.

He often repaints and reworks pieces (out of boredom or to test new ideas). His work isn't made to only sit in a gallery, but fills his life and his house. It's made to be used. Visiting Dawit's house, you are surrounded by his work - from the cluster of sculptures greeting you at the front door to the coffee table and mesob in high rotation in the loungeroom to the 2D clad walls. There is no preciousness, each piece is woven into daily life and reworked when it no longer fits.

Much of Dawit's work incorporates traditional Ethiopian elements but with his own unique interpretations of colour, pattern and material. He continues to create his work from found materials, sourcing from his workplace, the tip and beyond. Included in this exhibition are works made from pool noodles, Christmas baubles, thermal blankets, packing cardboard and even recycled industrial glue.

Dawit says of his work "I try to do different things. It's our culture, different craft...When I finish my job I'm tired, but I'm happy when I create my artworks. It's not for business, I'm happy if I sell, but happy when I do these paintings."

- Curated by **Nadia Refaei** and **Sharifah Emalia Al-Gadrie**

The artist, curators and Constance ARI work across Country cared for by the Palawa people of lutruwita. We acknowledge the Traditional Custodians of Country throughout so called 'Australia', as well as First Nations people from elsewhere, and their deep connection to the lands, skies and waterways over which sovereignty was never ceded. We pay our respect to all Elders; we are grateful for their continued sharing of knowledge and Culture.

አርቲስቶቹ፣ ኪውሬተሮቹ እና ኮንስታስ ኤአርአይ (ARI) በሉትሩዊታ የፓላዋ ሕዝብ እንክብካቤ በሚደረግለት መላው አገር ይሠራሉ። በተለምዶ 'አውስትራሊያ' ለሚባለው አገር ባህላዊ ጠባቂዎች እና ተንከባካቢዎች መሆናቸውን እንገነዘባለን፤ እንዲሁም በሌሎች ስፍራ የሚገኙትን የመጀመሪያዎቹን የህገሬው ሰዎች (First Nations people) በጥልቀት ከመሬቱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት፣ ከሰማያት እና ከወንዞች ጋር ያላቸው ቁርኝት በፍጹም እንዳልተበጠሰ እናውቃለን፡፡ ለአዛውንቶች አክብሮታችንን እንሰጣለን፤ በቀጣይነት ለሚያካፍሉን እውቀትና ባህል እናመሰግናለን።

constanceari.org

SUPPORTED BY

Tasmanian Government

ዳዊት ደርሶልኝ እራሱን እንደ አርቲስት አይቆጥርም፡፡ በልጅነቱ የአርት ሥራን ሙከራ አድርጓል፤ ከነዚህም መካከል የእንጨት ሥራና የብረት ሥራ ይገኙበታል፡፡ ይሁን እና፣ ይህንን ልምድ በእደገቱ ጊዜ አልቀጠለውም፡፡ በ1986፣ እንደታዳጊ ወጣት በሱዳን ስደተኞች ካምፕ በሚኖርበት ጊዜ፣ ዳዊት ከአለም አቀፉ አዳኝ ኮሚቴ (International Rescue Committee) ጋር በሚሰራበት ወቅት እንደገና ጀመረ፡፡ ለሁለት አመት ትምህርታዊ ምስሎችን ለትምህርት አቅርቦት ማእከል (Education Resource Centre) በመሳል ላይ ቆየ፡፡ ዳዊት እስከ 2017 ለላይፍ ራፍት ታዝሜኒያ (Life Raft Tasmania) መሥራት እስከጀመረበት ሂዜ ድረስ  ምንም አይነት ሥራ ሳይሰራ ቆይቶአል፡፡ በሥራ ቦታዎች የሚጣሉ የተለያዩ ቁሳቁሶችን በማየት የተጣሉትን ቁሳቁሶች ደግሞ በመጠቀም የተለያዩ የአርት ሥራዎች የመሥራት ልምምድ ጀመረ፡፡

የዳዊት የአርት ሥራዎች ከልምምድ ጋር የተያዙ ናቸው፤ ጨዋታን የተላበሰ ውጤት የማምጣት ፍላጎትን ጨምሮ፡፡ ስለሥራዎቹ ሲናገር፣ አብዛኛውን ጊዜ ሥራውን የሚጀምረው እጁ ላይ በሚገኙት ቁሳቁሶች ሲሆን፣ በድጋሚ ጥቅም ላይ ለማዋል የሰበሰባቸውን ቁሳቁሶች በመጠቀም የት እንደሚያደርሰው ይሞክራል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የአርት ሥርዎቹን በመደጋገም ይስላል (ከመሰልቸት ወይም አዳዲስ ሃሳቦችን ለመሞከር)፡፡ ስራዎቹ በአርት አዳራሾች እንዲቀመጡ ብቻ ሳይሆኑ ህይወቱን እና ቤቱን ይሞሉለታል፡፡ የሚሰሩት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ነው፡፡ የዳዊትን ቤት ሲጎበኙ በአርት ሥራዎቹ ይከበባሉ፡፡ ገና ሲገቡ ሰላምታ ከሚሰጥዎት የቅርፅ ምስል ጀምሮ በሳሎኑ ውስጥ የሚሽከረከሩት የቡና ጠረጴዛው እና መሶብን ጨምሮ በግድግዳው ላይ በ2D ያታያሉ፡፡ ድንቅ ነው የሚባል ነገር የለም፣ እየአንድ አንዱ ሥራ ከእለታዊ ህይወት ጋር የተሳሰረ እና ከቦታው ጋር የማይስማማ ካልሆነ በየጊዜው እንደገና ይሠራል፡፡

አብዛኛዎቹ የዳዊት ሥራዎች የኢትዮጵያን ባህላዊ ነገሮችን ያካታቱ ሲሆኑ የራሱ የሆኑ ልዩ የቀለም ትርጉሞች፣ ቅላፄ እና ቁሶች አሏቸው፡፡ ስራዎቹን በቀጣይነት የሚፈጥረው ከሚሠራበት ቦታ እና እቃዎች ከሚጣሉበት ሥፍራ ከተለቃቀሙ ቁሳቁሶች ነው፡፡ በእዚህ ኤግዚቢሽን ከተካተቱት መካከል፣ የዋና ሥፍራ ኑድልስ (pool noodles) የገና በብልስ (Christmas baubles)፣ ሙቀት ሰጪ ብርድ ልብሶች (thermal blankets)፣ የማሸግያ ካርቶኖች እና በድጋሚ ሥራ ላይ እንዲውል የተደረገ ማጣበቂያንም (industrial glue) ይጨምራል፡፡

ዳዊት ስለሥራው እንዲህ ይላል፣ "የተለያዩ ነገሮችን ለመሥራት እሞክራለሁ፡፡ የተለያዩ ጥበባት ባህላችን ነው..... ሥራዬን ስጨርስ ይደክማኛል፣ ቢሆንም በምፈጥራቸው የአርት ሥራዎች እደሰታለሁ፡፡ ለንግድ አይደለም፣ ቢሸጡልኝ ደስ ይለኛል፣ ነገር ግን ስእሎቹን በምሰልበት ወቅት ደስተኛ ነኝ፡፡

- በናዲያ ራፋኢ (Nadia Refaei) እና ሻሪፋ ኢማሊያ አል-ጋድሪ (Sharifah Emalia Al-Gadrie) የቀረበ

The first thing that strikes me about Dawit Dersolign's works is how intricate they are. Dawit has an acute eye for detail. Maximalist in their aesthetic, his works communicate his artistic passion and drive to create wonderful things. Pool noodles, recycled cardboard, Christmas baubles and sponges are just some of the materials utilised in his highly prolific and expressive art practice.

Dawit began working at Life Raft Tasmania in 2017. He was not regularly painting or making work at the time, but instead he saw the artistic potential in the materials around him. He began making art from these industrial supplies that would otherwise be thrown away and destined for landfill. Dawit speaks passionately about the industrial glue that helps bind his works, as well as his appreciation of his co-workers who keep materials aside for him to make his art.

When first viewing Dawit's artworks, I was reminded of the video game, De Blob. In this game, characters bring colour to a world of a greyscale palette, after you see its life and vitality being sucked from the screen. Through continuing the game, you begin to see the environment from a new perspective, with the main character gradually adding colour to the parts of the city they touch and move through.

I think the visual and emotional impact of viewing Dawit's works functions in a similar way to the premise of De Blob. They bring colour, life, and energy to the world. To experience Dawit's works is to feel alive, and to feel warmth in a world that at times, can feel monotonous and bleak. I feel invigorated seeing Dawit's works. They allow me to see the world in a renewed and energising manner, and I carry this feeling with me whenever I think of them.

This exhibition features new works by Dawit after his previous show at Moonah Art Centre in 2021. As well as including paintings and abstract colourful sculptures, there are a variety of objects in this exhibition that Dawit has made showcasing Ethiopian culture. Many of these artworks also have functional components, including to hold food and beverages, as well as musical instruments and traditional chairs. The show is interactive, with these objects part of spaces where people can interact and enjoy the company of others.

የዳዊት ደርሶልኝ ሥራዎች በቅድሚያ ከሚያስደንቁኝ ጉዳዮች በጣም ውስብስብ መሆናቸው ነው። ዳዊት ለዝርዝር ጉዳዮች ጥሩ አይን አለው። በጥራታቸው ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው፣ ሥራዎቹ የአርት ችሎታውን የሚገልጹ እና ለሥራው ከፍተኛ ስሜት እንዳለው የሚገልጹ እና ግሩም የሆኑ ሥራዎች እንዲፈጥር ይገፋዋል። የመዋኛ ቦታዎች የመንሳፈፊያ ኑድልስ፣ በድጋሚ ሥራ ላይ የዋሉ ካርቶኖች፣ የገና መብራቶች እና እስፖንጆች ከሚጠቀምባቸው ቁሳቁሶች ጥቂቶቹ ሲሆኑ በጣም ብርካቶች እና ገላጭነት ያላቸው የአርት ልምዶች ናቸው።

ዳዊት ሥራውን በላይፍ ራፍት ታዝማኒያ (Life Raft Tasmania) በ2017 ጀመረ። በዚያን ጊዜ በተካታታይ አይስልም ወይም ሥራዎቹን አየፈጥረም ነበር፣ ነገር ግን በአካባቢው የሚገኙትን ቁሳቁሶች ለአርት ሥራ ግብአት ሊኖራቸው የሚችለውን አስተዋጽኦ ያገናዝብ ነበር። ከነዚህ ሊወረወሩ ከነበሩ የኢንዱስትሪ ውዳቂዎች አርት መሥራቱን ጀመረ። ዳዊት ሥራዎቹን ስለሚያስተሳስርለት የኢንዱስትሪ ሙጫ (ማጣበቂያ)  በስሜት ከመናግሩም በበለጠ፣ ለሥራው የሚጠቀምባቸውን ውዳቂ እቃዎች ወደ ጎን በማስቀመጥ የሚረዱትን አብረውት የሚሠሩትን ሰዎች በጣም ያመሰግናል።

የዳዊትን የአርት ሥራ ለመጀመሪያ ጊዜ ስመልከት፣ ደ ብሎብ (*De Blob*) የተሰኘውን የቪድዮ ጨዋታ አስታወሰኝ። በጨዋታው ላይ፣ ከእስክሪኑ ላይ ሕይወቱ እና አስፈላጊነቱ ከተሚጠጠበት በኋላ፣ ግራጫነቱን ቀይሮ ወደ ቀለማማነት መመለሱን ያስታውሰኛል። ጨዋታውን ሲቀጥሉ፤ አካባቢውን በአዲስ መልክ ማየት ይጀምራሉ፣ ዋነኞቹ ተዋንያን ቀስ በቀስ በከተማው አንዳንድ ቦታዎች የነኩትን ቦታዎች ቀለሙን እየቀየሩ ያልፋሉ።

እንደሚመስለኝ፣ የዳዊት ሥራ  በእይታና በስሜት ላይ የሚያመጣው ለውጥ ከደ ብሎብ የቪዲዮ ጨዋታ ጋር ተመሳሳይነት አለው። ለዓለም ቀለም፣ ሕይወት እና ጉልበት ይሰጣሉ። ከዳዊት ሥራ ልምድ ማግኘት ማለት ህያው የመሆንን ያህል ስሜት፣  እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ በሚሰለች እና ጨለማ በሚመስል ዓለም ሞቅታ ያሰማል። የዳዊትን ሥርዎች ሳይ እነቃቃለሁ። ዓለምን በታደሰ እና በተጠናከረ መንገድ እንዳይ ያደርጋኛል፣ እናም ስለሥራዎቹ በማስብበት ጊዜ ሁሉ ስሜቱን ይመጣብኛል።

ይህ ኤግዚቢሽን ዳዊት በ2021 በ ሙናህ አርት ማከል *(Moonah Art Centre* in 2021) ካሳየው በተለየ አዳዲስ ሥራዎቹን ያቀርባል። እንዲሁም የአርት ስእሎቹን እና አብስትራክት ባለቀለም ቅርጻቅርጾችን እንዲሁም ዳዊት የኢትዮጵያን ባህል የሚያሳይባቸው የተለያዩ እቃዎችን ያቀርባል። አብዛኛዎቹ የአርት ሥራዎቹ ሥራ ላያ የሚውሉ ሲሆኑ፣ እንደ ምግብ እና መጠጥ መያዣ ብሎም የሙዚቃ መሳሪያዎች መያዣና ባህላዊ ወንበሮችን ያካትታል።

An example of Dawit's intention to share aspects of Ethiopian culture through his art, is the way Dawit has incorporated traditionally inspired patterns and colours into his interpretation of the mesob, a basket traditionally woven from grass. The materials Dawit uses are unique. In one of his mesob works, he covered the surfaces with a range of materials including rope, silver quilted fabric and magnificently threaded glossy beads. These unconventional materials harmoniously work together to form patterned sections of glistening colour.

When I visited Dawit at his home I found it amusing to hear about the objects he had repainted since curators Nadia Refaei and Sharifah Emalia Al-Gadrie had last visited. Dawit primarily reworks pieces due to boredom, or the desire to try new things. He starts with a material and sees where his inspiration takes him.

It is interesting that Dawit does not call himself an artist. When I saw his works and asked, "is this your studio?" he laughed. Dawit is a friendly and inviting person, and his workspace similarly reflects his personality. His passion for colour, pattern, and texture is also evident, with the space featuring sheer and patterned fabrics suspended from the ceiling, as well as red tinsel beaming in the corner of the room.

On this occasion, I could hear water trickling down from inside the centre of a fountain handmade by Dawit. Lights sprung from inside this structure, delivering a calming effect as the colours interacted with the water in front of a beautifully painted waterfall scene. A brightly coloured modular screen stood nearby, with an arrangement of climbing green leaves and flowers similarly lit by disco-esque colours around them. It's in this space where he creates, but it's also much more than that. This place is for making, a place for connection, and for celebrating both internal and external environments.

Dawit's practice captures the fun and immersive potential in the everyday materials he seeks out. I want to take in every detail of these intricate works, and I want to gain access to the stories behind their making. There's something utopian about Dawit's works. Viewing Dawit's works can help to make our everyday experiences and future engagements with art even more spectacular, meaningful, and inviting.

–**Jade Irvine**, artist and writer

ኤግዚቢሽኑ ለመወያየት እና ለመነጋገር የሚይስችል ሆኖ ስለተዘጋጀ ከሌሊች ጋር በመሆን እንዲደሰቱ ያስችልዎታል;፡

እንደ ምሳሌ፣ የዳዊት የኢትዮጵያን ባህል በአርት ሥራው በኩል የማሳየት ፍላጎት ባህላዊ በሆነ መንገድ የተነሳሳውን ቅርጽ እና ቀለማትን በማስተሳሰር፣ እንደመሶብ ባሉት የኢትዮጵያ የባህል ውጤቶች ጋር በማያያዝ ይገልጻቸዋል። ዳዊት የሚጠቀምባቸው ቁሳቁሶች የተለዩ ናቸው። በአንዱ የመሶብ ሥራው ላይ፣ የመሶቡን አካል በገመድ፣ በብር የተገመዱ ሸማዎች፣ በክር የተያያዙ የሚያብለጨልጩ ዛጎሎችን ጨምሮ በተለያዩ ቁሶች ሸፍኖታል። እነዚህ ያልተለመዱ ቁሳቁሶች በአንድነት ተጣምረው በሚያብለጨልጩ ቀለማት የታጀቡ ቅርጾችን ፈጥረዋል።

ዳዊትን በቤቱ በጎበኘሁበት ወቅት፣ ባለፈው ጊዜ ኩሬተር ራፌ እና ሻሪፋ ኢማልያ አል-ጋድሪ ከጎበኙት በኋላ እንደገና የሳላቸውን እቃዎች አይቼ በጣም ተገርሜአለሁ። ዳዊት በመሰለቸት ወይም የተሻለ አዲስ ነገር ለመፍጠር ባለው ፍላጎት የተነሳ ሥራዎቹን በድጋሚ ይሰራቸዋል። በእቃዎች ይጀምርና መነሳሳቱ ወዴት እንደሚወስደው ያያል።

ዳዊት እራሱን አርቲስት ብሎ ያለመቁጠሩ የሚገርም ነው። ሥራዎቹን ባየሁበት ጊዜ "ይህ ስቱዲዮህ ነው?" ብዬ ስጠይቀው፣ ሳቀ። ዳዊት በጣም ሰውን ያቀርባል እናም ጋባዥ ግለሰብ ነው ስለሆነም የሥራ ቦታው በተመሳሳይ ማንነቱን ያንጸባርቃል። ለቀለማት፣ ለንድፍ እና ለቴክስቸር ያለው ከፍተኛ ስሜት ግልጽ ነው። ይህም በቅርጻቅርጽ ታጅበው ከጣራ በተንጠለጠሉት እና በክፍሉ ማእዘን ቀያይ የቲንስል ቋሚዎች የሚታዩት አርቶች ያለውን ከፍ ያለ ስሜት ይገልጻሉ።

በዚህ ወቅት፣ ዳዊት በእጁ በሰራቸው ምንጭ መሰል አርቶች ውስጥ ውሃ ሲፈስ ይሰማኛል። ብርሃንም ከመካከሉ በውስጥ በኩል ሲበራ ሲታይ ከፊት ከሚታየው የውሃ ፏፏቴ እይታ አርት ጋር ሲጣመር የማረጋጋት ስሜት ይሰጣል። ብሩህ የሆነ በሞዱላር ስክሪን ላይ ከሚወጡት አርንጓዴ ቅጠሎች እና አበባዎች በዲስኮ-ኤስኪ ተከበው በቅርበት ቆመዋል። በዚህ ቦታ ነው የፈጠራ ሥራውን የሚከውነው፣ ነገር ግን ከዚያም በላይ ነው። ይህ ቦታ የመሥሪያ ነው፣ የግኙነት እንዲሁም የውስጥ እና የውጪ አባባቢዎች የሚከበሩበት ስፍራ ነው።

የዳዊት ተለምዶ ደስታን ይይዛል እንዲሁም በየእለቱ የሚፈልጋቸው ቁሳቁሶች የመመሰጥ ችሎታ አላቸው። የዚህን ውስብስብ ሥራ ዝርዝር ለመውሰድ እፈልጋለሁ፣ እንዲሁም ከሥራዎቹ ጀርባ ያልውን ታሪክ ጨምሮ። የዳዊት ሥራዎች ምናባዊነት ያላቸው ይመስላል። የዳዊትን ሥራዎች ማየት የእለት ተእለት ልምዶቻችንን እና የወደፊት አርትን በተመለከተ ለምናደርጋቸው ሥራዎች በጣም አስደናቂና ትርጉም ያለው እና ጋብዥ ያደርጋቸዋል።

ጄድ ኧርቫይን፣ አርቲስት እና ጸሐፊ